የትራንስፖርት ሚኒስቴር
MINISTRY OF TRANSPORT

# የሎጀስቲክስ ዘርፍ ፖሊሲ

## በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሚንስትሮች ም/ቤት የጸደቀ

ግንቦት 2012 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# ማውጫ

ትርጉም ........ 3
አጽህሮተ-ቃላት ........ 4
መግቢያ ........ 5
ክፍል አንድ ........ 6
ጠቅላላ ጉዳዮች ........ 6
1.1. አጠቃላይ ሁኔታ ........ 6
1.2. የፖሊሲው መነሻዎች ........ 8
1.2.1. ብሔራዊ የትራንስፖርት ፖሊሲ ........ 8
1.2.2. ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ........ 8
1.2.3. የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ........ 9
1.2.4. የግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ ........ 9
1.2.5. የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ልማት ፖሊሲ ........ 10
1.2.6. ብሔራዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፖሊሲ ........ 11
1.2.7. የሀገራችን የሎጂስቲክስ አገልግሎት አከናዋኞች ........ 11
ሀ. የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት አገልግሎ ድርጅት /ኢባትሎአድ/ ........ 11
ለ. የግል ባለሃብቱ ........ 12
ክፍል ሁለት ........ 13
የፖሊሲው ራዕይ፣ ዓላማዎች፣ መርሆዎች እና አስፈላጊነት ........ 13
2.1. የፖሊሲው ራዕይ ........ 13
2.2. የፖሊሲው ዓላማዎች ........ 13
2.3. የፖሊሲው መርሆዎች ........ 13
2.4. የፖሊሲው አስፈላጊነት ........ 13
ክፍል ሦስት ........ 15
የፖሊሲ ጉዳዮች ........ 15
3.1. የሎጅስቲክስ ዘርፍ አደረጃጀት ........ 15
3.2. የሎጅስቲክስ ዘርፍ አገልግሎት ........ 16
3.3. የሎጅስቲክስ ዘርፍ አሰራር ........ 19
ክፍል አራት ........ 22
የፖሊሲ ማሳፈጸሚያ ስልቶች ........ 22

ክፍል አምስት ....................................................................................................................................24
ልዩ ልዩ ጉዳዮች ................................................................................................................................24
5.1. የፖሊሲው ክትትልና ግምገማ .......................................................................... 24
5.2. የባለድርሻ አካላት ሚና እና ተሳትፎ .................................................................. 24
5.3. ቀጣይ አቅጣጫዎች ....................................................................................... 24

# ትርጉም

FOB (Free On Board):- ማለት ገዥው በመረጠው አጓጓዥ ከመረጠው የወደብ መጫኛ ወደ መረጠው የባህር ወደብ መዳረሻ ዕቃ የሚጓጓዝበት ዓለም አቀፍ የግዥ ዘዴ /ተርም/ ነው፡፡

CIF (Cost Insurance Freight)፡- ማለት ሻጭ በመረጠው አጓጓዥ ገዢ ከመረጠው የወደብ መጫኛ ገዢ ወደ መረጠው የባህር ወደብ መዳረሻ ዕቃ የሚጓጓዝበት ዓለም አቀፍ የግዥ ዘዴ (ተርም) ነው::

Slot Charter Agreement (SCA)፡- ማለት ከመርከብ የተወሰነ ወይም ቢያንስ አንድ ባለ ሀያ ጫማ ኮንቴይነር ለማስቀመጥ የሚያስችል አንድ ወይም ከዚያ በላይ ቦታ በመከራየት እቃን በተለያዩ የመርከብ ኩባንያዎች ማጓጓዝ ነው፡፡

Shippers Council:- ማለት እቃ አስመጪዎችን፣ ላኪዎችን እና የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎችን ያካተተ ምክር ቤት ሲሆን የተለያዩ የሎጅስቲክስ ዋጋዎችን እና የጊዜ መጓተትን የሚቆጣጠር የግሉ ዘርፍ አደረጃጀት ነው፡፡

# አጽህሮተ-ቃላት

ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ = የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት

NVOCC = None Vessel Owner Common Carrier

IMO = International Maritime Organization

FOB= Free on Board

CIF= Coast, Insurance and Freight

# መግቢያ

የሎጂስቲክስ አገልግሎት በሀገራችን ውስጥ ለረዥም ዘመናት በአንጻሩ በቂ ትኩረት ሳይሰጠው የቆየ የአገልግት ዘርፍ ነው፡፡ የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ አስተማማኝነትና ዘላቂነት ከሚረጋገጥባቸው መለኪያዎች አንዱ ቀልጣፋና ውጤታማ የሎጂስቲክስ ስርዓት ነው፡፡

የኢትዮጵያ የሎጂስቲክስ ስርዓት እንደ አንድ የአገልግሎት ዘርፍ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶት መተግበር ከጀመረ የተወሰኑ ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ ይህም የሀገራችን የሎጂስቲክስ አገልግሎት ገና ያልጎለበተ እና ከኢኮኖሚያችን እድገትና ፍላጎት አንጻር ደግሞ በእጅጉ ብዙ መሻሻል እንደሚቀረው ያመለክታል፡፡

የሎጂስቲክስ አገልግሎት ዘርፉን በስርዓት ለመምራትና አገልግሎቱ ቀልጣፋ ሆኖ የሃገራችንን ኢኮኖሚ ሊያግዝ በሚገባው ደረጃ እንዲደራጅ ለማድረግ ደግሞ በብሄራዊ ደረጃ የሎጂስቲክስ ዘርፉ የሚመራበትን ግልጽ የፖሊሲ አቅጣጫ መቅረጽና ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እስከአሁን ድረስ ያለው የሎጂስቲክስ አፈጻጸም በግልጽ በታወቀ የፖሊሲ አቅጣጫ የሚመራ ባለመሆኑ አገልግሎቱ የተቀናጀና ቀልጣፋ ካለመሆኑም በላይ በውድድር ላይ ያልተመሰረተ፤ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ያልተደገፈና ለአገልግሎቱ እጅግ መሰረታዊ የሆነው የመረጃ ፍሰቱ ኋላ ቀር የሚባል በውድድር የሚገኝ ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች የማይንጸባረቁበት በመሆኑ የሎጂስቲክስ ዘርፉ የሀገራችንን የኢኮኖሚ እድገት ከመደገፍና ከማቀላጠፍ አንጻር መሰረታዊ ማሻሻያዎች ሊደረጉበት ይገባል፡፡

በእርግጥ መንግስት በ2011 ዓ.ም ይህን ዘርፍ ለማዘመንና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆን ለማስቻል የሎጂስቲክስ ስትራቴጂ ሰነድን አጽድቋል፡፡ ይህ የሎጂስቲክስ ስትራቴጂ ሰነድም የፖሊሲ ጉዳዮችን በተመለከተ በቀጣይ የመንግስትን አቅጣጫ ያመላከተ ሲሆን በስትራቴጂው በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በሎጅስቲክስ ዘርፍ ያሉ ፖሊሲ ነክ ጉዳዮች በግልጽ ቀርጸና አቅጣጫ አስቀምጦ መወሰን በማስፈለጉ ይህ ፖሊሲ ተዘጋጅቷል፡፡ የፖሊሲ ሰነዱ ከስትራቴጂ ሰነዱ ጋር የማይቃረን እና ይልቁንም የስትራቴጂ ሰነዱን አተገባበር በሚገባ ፈር የሚያስይዝ ነው፡፡

ስለሆነም የሎጂስቲክስ ስትራቴጂ ሰነዱ ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ፖሊሲ ኢትዮጵያ በሎጂስቲክስ ስርዓት ማዘመንና ዘርፉ ለተለያዩት የኢኮኖሚና ሃገራዊ ጉዳዮች ሊያበረክት የሚገባውን የአገልግሎት ደረጃ ለማሳካት የሚያገለግል ይሆናል፡፡

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ ጉዳዮች

## 1.1. አጠቃላይ ሁኔታ

በመግቢያው ላይ እንደተመለከተው የሀገራችን የሎጂስቲክስ ዘርፍ ከጊዜ ወደጊዜ አስፈላጊነቱ እየጎለበተና ቁልፍ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ መሆኑ ትኩረትን ያገኘ የአገልግሎት ዘርፍ ሲሆን በተለይ አሁን ደግሞ እንደ አንድ የአገልግሎት ዘርፍ እራሱን ችሎ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ለዚህ የዘርፉ ቀደም ሲል ተገቢውን ትኩረት አለማግኘት በርካታ ጉዳዮች እንደምክንያትነት ሊጠቀሱ ቢችሉም የአገልግሎት ዘርፉ ለአጠቃላይ የኢኮኖሚያችን እድገት ያለውን ቁልፍ ሚና በወጉ ካለመረዳት የሚመነጨው ምክንያት ዋናው ስፍራ ይይዛል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝ ሌሎች ነባራዊ የሃገራችን ሁኔታዎችም ለዘርፉ አለመጠንከር አስተዋጽኦ ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ለአብነት ያህልም ዘርፉ በዋናነት ሊቀላጠፍ የሚችለው መሠረተ-ልማት ማለትም የመንገድ፣ የባቡር፣የደረቅ ወደብ፣ የሥርጭት መዕከላት፣ መጋዘን የተሟላና የተቀናጀ ሲሆን ነው፡፡ በሃገራችን የነበረው የመንገዶችና የባቡር መሰረተ-ልማት ከጥራትም ሆነ ከሽፋን እንዲሁም እርስ በርሱ ተመጋጋቢ ከመሆኑ አንጻር በቂ በሚባል ደረጃ የለማ ስላልነበረ የሎጂስቲክስ ስርዓቱ እንዳይጎለብት አንደ ምክንያት ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

በሌላ በኩል የሃገራችን የምርት ስፍራዎችና ገበያዎች ወይንም ምርቶቹን በግብዓትነት የሚጠቀሙ ማምረቻዎች ለግብይት አመቺ በሚባል ደረጃ የተሳሰሩ አይደሉም፡፡ በመሆኑም የሎጂስቲክስ ስርዓቱ ይህን ጥምረት በሚያጠነክር መልኩ አገልግሎት ሲሰጥ አልነበረም፡፡

ሃገራችን ኢትዮጵያ ወደውጭ ሃገር የምትልካቸው የንግድ ምርቶችን በተመለከተም የሎጂስቲክስ ስርዓቱ ዘመናዊና ቀልጣፋ አሰራሮችን በሚፈለገው ደረጃ ሲከውን አልነበረም፡፡ በተለይም የጭነት ማጓጓዝ ስርዓት፣ የመጋዘን አገልግሎት፣ አስተሻሸጎች፣ የጭነት እቃዎችን ዝውውር በተመለከተ ሊኖር የሚገባው የመረጃ ፍሰት ወዘተ .... ትኩረት ተሰጥቷቸው ሲተገበሩ የቆዩ ጉዳዮች አልነበሩም፡፡ ሃገራችን ውስጥ ያሉት የሎጂስቲክስ አገልግሎት

Ministry of Transport

አከናዋኞች ያሏቸው የሎጂስቲክስ ማከናወኛ ሃብቶችም እንዲሁ በሚገባ የተደራጁ፣ እርስ በርስ የተቀናጁና መረጃ የሚለዋወጡ አልነበሩም፡፡

በተለይ ደግሞ በዘርፉ ሊኖር የሚገባው የሰለጠነና የተማረ የሰው ኃይል እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ትስስር በየጊዜው እየዘመነ ከመጣው የዘርፉና የቴክኖሎጂ ቅንጅት አንጻር ውሱን ነው ለማለት ይቻላል፡፡

ይህ አጠቃላይ የሎጂስቲክስ ስርዓቱ ሁኔታ መሰረታዊ ለውጥ ካልተደረገበት ደግሞ ለኢኮኖሚው እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከማበርከት ይልቅ በተቃራኒው እንቅፋት እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል፡፡ በመሆኑም ይህ ፖሊሲ ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ ይህን መሰረታዊ ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል ይሆናል፡፡

ይህ ማለት ግን የሎጂስቲክስ ዘርፉ እስከአሁን ባለው ውሱን የአፈጻጸም ደረጃም ቢሆን ለሀገራችን ኢኮኖሚ እየተጫወተ የሚገኘው ሚና ከቁጥር የሚገባ ነው ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም የእስካሁኑ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ስርዐታችን ለሀገራችን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ /GTP/ መሳካት የማይናቅ አስተዋጽኦ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ የዕድገትና ትረራንስፎርሜሽን ዕቅዱ አንዱ ግብ የሀገራችንን የወጪ ንግድ ማጎልበት ነው፡፡ የወጪ ንግዳችንን ለማጎልበት ከሚያስችሉን መሰረታዊ ተግባሮች ውስጥ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ስርዓታችን አንዱና የጎላ ስፍራ የሚሰጠው ነው፡፡ የሎጂስቲክስ ስርዓት ሲባል ደግሞ ከጭነት ትራንስፖርት አገልግሎት ባለፈ የመጋዘን፣ የዕቃ መስተላለፍ፣ የጉምሩክ ማስተላለፍ፣ የወደብ አገልግሎት ጉዳዮችን አጠቃልሎ የያዘና በግልጽና ቀልጣፋ የመረጃ ስርዓት የተደገፈ አገልግሎት ነው። ስለሆነም የሀገራችንን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ /GTP/ ከማሳካት አንጻር የሎጂስቲክስ አገልግሎት ስርዐታችን ትንሽ የማይባል ድርሻውን ሲወጣ ቆይቷል፡፡

ከአጠቃላይ የሀገራችን የኢኮኖሚ እንቅስቃስ አንጻርም ቢሆን የሎጂስቲክስ ስርዐታችን ወሳኝ ሚና አለው፡፡ የሀገራችን ኢኮኖሚ መሠረት ለሆነው የግብርና ሴክተር ግብዓቶችን በወቅቱና በሚፈለገው መጠን ለተጠቃሚው ከማድረስ ጀምሮ ምርቶች ከደረሱ በኋላም ወደሚፈለገው የገበያ መዳረሻቸው ከማድረስ አኳያ፣ የማኑፋክቸሪን ኢንዱስትሪ ግብዓቶችንና የምርት ውጤቶችን ከማመላለስ አኳያ፣ የገቢና የወጪ ንግዶችን ከማቀላጠፍ አኳያ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ዘርፉ ሰፊ አገልግሎቶችን እየሰጠ ይገኛል፡፡



Ministry of Transport

ነገር ግን የሀገራችን ኢኮኖሚ እድገት ከሚፈልገው እና በዘርፉ ተወዳዳሪነትን አረጋግጦ የመሪነት ስፍራን ለመያዝ ገና በርካታ ተግባራት ሊከናወኑ ስለሚገባ ይህን አጠቃላይ አቅም በሚያጎለብት መልኩ የሎጂስቲክሱን ቀጣይ አቅጣጫ እንዲመራ ይህ የፖሊሲ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

## 1.2. የፖሊሲው መነሻዎች

### 1.2.1. ብሔራዊ የትራንስፖርት ፖሊሲ

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የትራንስፖርት ሚኒስቴር አዘጋጅነት ብሔራዊ የትራንስፖርት ፖሊሲ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

በብሄራዊ የትራንስፖርት ፖሊሲው ላይ ከተካተቱት ዋና ዋና ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ዘርፍ ነው፡፡ በእርግጥ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ከትራንስፖርት አገልግሎትም ላቅ ያለ እና እንደ መጋዘን አገልግሎት፣ የዕቃዎች ማስተላለፍ አገልግሎት፣ የደረቅ ወደብ አገልግሎት፣የጉምሩክ አሠራር፣የፋይናስ ሥርዓት፣ የንግድ ሥርዓት ወዘተ ጉዳዮችን አካትቶ የያዘ ልዩ የአገልግሎት ዘርፍ ሲሆን ዘርፉ በአጠቃላይ የሚመራበት የፖሊሲ አቅጣጫ ከብሔራዊ የትራንስፖርት ፖሊሲው ጋር የተቆራኘ መሆኑ እሙን ነው፡፡

ይህ የሎጂስቲክስ ፖሊሲም ይህን መሰረታዊ የትራንስፖርት ፖሊሲ መነሻ አድርጎ የተዘጋጀ ነው፡፡

### 1.2.2. ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም

የኢትዮጵያ ሀገራችንን የኢኮኖሚ ዕድገት በአጭር ጊዜ ውስጥ ትራንስፎርም ለማድረግ እንዲረዳ ታስቦ የተዘጋጀው አንዱ ጉዳይ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ነው፡፡ ከዚህ የኢኮኖሚ ማሻሻያ መሠረታዊ ጉዳዮች ውስጥ ደግሞ የሀገራችንን የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ለውድድር ክፍት በማድረግ የግል ባለሃብቱ እና ሌሎች የኢኮኖሚ አክናዋኞች እንዲሳተፉ በማድረግ እያንዳንዱ ዘርፍ ከውድድር የሚገኘውን የቅልጥፍና፣ የቴክኖሎጂ፣ የሥራ ዕድል ፈጠራ፣ የዕውቀት ሽግግር እና የአቅርቦት አቅምን ማሳደግ ጥቅሞች በማስገኘት ኢኮኖሚው በአስተማማኝ የዕድገት መሰረት ላይ የተገነባ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡

ምንም እንኳን የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው ለአጭር ጊዜ የተቀረጸ ቢሆንም ከአቅጣጫ አንጻር የሀገራችን ኢኮኖሚ የሚሻሻልበትን አግባብ በግልጽ የሚያሳይ እንደመሆኑ ለሎጂስቲክስ ፖሊሲው እንደ አንድ መነሻነት ተወስደል፡፡ በተለይም የሎጂስቲክስ ዘርፉ ቁልፍ የኢኮኖሚያችን አቀላጣፊ አገልግሎት እንደመሆኑ በዚህ ንዑስ-ዘርፍ የመንግስት ድርሻ፣ ሚና እና ተሳታፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ዘርፉን ለውድድር ክፍት ማድረግ፣ የግል ባለሃብቱን ተሳትፎ ማጎልበትና የዘመናዊ አሰራርና ቴክኖሎጂ አስተዋጽኦን ለዘርፉ ዋና ማቀላጠፊያ ግብዓት ማድረግ መሰረታዊ የፖሊሲው አካሎች ስለሆኑ ከዚህ አንጻር ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ለዚህ የሎጂስቲክስ ፖሊሲ እንደ መነሻ ተወስደዋል፡፡

### 1.2.3. የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ

ለዚህ የሎጂስቲክስ ፖሊሲ መነሻ የሆነው ሌላኛው ጉዳይ የኢንዱስትሪ ልማት ፖለሲ ነው፡፡ በዚህ የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ውስጥ አንዱ ዋና ጉዳይ ሆኖ በተለይ የተገለጸው አስተማማኝ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ሥርዐት መዘርጋት ነው፡፡

አስተማማኝ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ሥርዐት ደግሞ የትራንስፖርት አገልግሎትን፣ የመጋዘን አገልግሎትን፣ የደረቅ ወደብ አገልግሎትን ወዘተ ….. ጉዳዮች ያጠቃልላል፡፡ የዚህ የሎጂስቲክስ አገልግሎቶች ዓላማ ደግሞ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን እና ምርቶችን በወቅቱና በቅልጥፍና የሚፈለገውን የሎጂስቲክስ አገልግሎት መስጠት ሲሆን ከዚህ ባልተናነሰ መልኩ ግብዓቶቹና ምርቶቹ ሲጓጓዙም ሆነ በጉዞ ሂደት የመጋዘን ወይም ተመሳሳይ ቆይታ ተገቢው ጥንቃቄና ቅልጥፍና እንዲኖራቸው ይፈለጋል፡፡

ይህን የፖሊሲውን ዓላማ ለማሳካት ደግሞ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ያለው ተሳትፎ ጉልህ ነው፡፡ እናም የሎጂስቲክስ ዘርፉ ይህን የሚጠበቅበትን ጉልህ ሚና በአግባቡ መወጣት እንዲችል ከሌሎች ፖሊሲዎች በተጨማሪ ከኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ጋር የተጣጣመ የሎጂስቲክስ ፖሊሲ መቅረጽና መተግበር አስፈልጓል፡፡ በመሆኑም የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ለዚህ ፖሊሲ አንዱ መነሻ ተደርጎ ተወስዷል፡፡

### 1.2.4. የግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ

ልክ እንደ ኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲው ሁሉ የግብርናና ገጠር ልማት ፖሊሲውም የግብርና ምርቶች ግብዓቶችን አቅርቦት፣ የመጋዘን አገልግሎት፣ የእቃ ማስተላለፍ አገልግሎት፣

Ministry of Transport Archive

ቀልጣፋ የደረቅ ወደብ አገልግሎት፤ የግብርና-ገበያ እና የግብርና-ኢንዱስትሪ ትስስርን ዋና መሰረት አድርጎ የተቀረጸ ፖሊሲ ነው፡፡ ግብርና የሀገራችን ዋና የኢኮኖሚ አውታር እንደመሆኑ የግብርናውን ልማት ያለ ዘመናዊና ቀልጣፋ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ሥርዐት ውጤታማ ማድረግ እንደማይቻል ግንዛቤ ተወስዷል፡፡

ግብርናውን ለማዘመን፤ የገጠሩን የግብርና አከናዋኞች እርስ በርስ ለማስተሳሰር፤ የግብርና ዋና ግብዓት የሆኑትን እንደማዳበሪያና ምርጥ ዘር የመሳሰሉትን በበቂ ሁኔታና በሚፈለገው ጊዜ ውስጥ ወደሚፈለግበት ስፍራ ለማድረስ የሎጂስቲክስ አገልግሎት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ የሚተካ አይደለም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የግብርና ምርቶችን በፍጥነትና በአስተማማኝ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ስርዓት ወደ ገበያ ወይም የግብርና ውጤቶችን ፈላጊ ወደሆኑ ኢንዱስትሪዎች ማድረስ የሚቻለውና ሀገራችን ከግብርናው ዘርፍ ልታገኝ የሚገባውን ጥቅም ማጎልበት የሚቻለው በሚገባ የተዋቀረና አስተማማኝ አደረጃጀት ያለው የሎጂስቲክስ አገልግሎት ሲኖር ነው፡፡ ይህን ለማረጋገጥ ደግሞ የሎጂስቲክስ ዘርፉ በፖሊሲ የተቀረጸ ግልጽ አቅጣጫና ግብ ሊኖረው ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ምክንያትም ይህ የሎጂስቲክስ ፖሊሲ የግብርናና የገጠር ልማት ፖሊሲን እንደመነሻ አድርጓል፡፡

### 1.2.5. የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ልማት ፖሊሲ

የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎችን ለማልማትና የሃገራችን አጠቃላይ እድገት ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማገዝ የሚረዳ ፖሊሲ ጸድቋል፡፡

ከፖሊሲው ዋና ጉዳዮች አንዱም የሀገራችን አርብቶ-አደርና ከፊል አርብቶ-አደር አካባቢዎች ከሚታወቁባቸው የተለያዩ የእንስሳት እርባታና ምርቶች ልማት እንዲጠቀሙ ማድረግ ነው፡፡ ይህን ለማሳካት ደግሞ እነዚህ የእንስሳት ምርቶች ወደገበያ በተለይም ወደውጭ ሃገር ገበያ በሚፈለገው ጥራትና ደረጃ እንዲቀርቡ ማድረግ ነው፡፡

ይህን የምርት አቅርቦት ለማቀላጠፍና ለምርቱ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማሳደግ የሎጂስቲክስ ስርዓቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በመሆኑም የሎጂስቲክስ ፖሊሲው የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ልማት ፖሊሲውን ታሳቢ አድርጓል፡፡

Ministry of Transport

### 1.2.6. ብሔራዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፖሊሲ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. መንግስት የኢንፎርሜሽን እና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፖሊሲና ስትራቴጂ ጸድቋል፡፡ ከዚህ ፖሊሲ ግቦች ውስጥ አንዱና ዋናው የመንግስት የአገልግሎት መሰረተ-ልማቶችን ማዘመንና በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የተደገፉ በማድረግ ከአገልግሎት ዘርፉ የሚገኘውን የኢኮኖሚ ጥቅምና አስተማማኝነት ማረጋገጥ ነው፡፡

የሎጂስቲክስ ዘርፍ ደግሞ የአገልግሎት ዘርፍ እንደመሆኑ የዘርፉ ዋና የደም ስር የሆነው ጉዳይ የመረጃ ፍሰትና አስተማማኝነት ነው፡፡ የሎጂስቲክስ ዘርፍ በባህሪይው መረጃን መሰረት ያደረገ የአገልግሎት ዘርፍ ነው፡፡ ዘርፉን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ማዘመንና ማደራጀት ካልተቻለ የሎጂስቲክስ አገልግሎቱን ውጤታማ ማድረግ አይቻልም፡፡

በመሆኑም በሎጂስቲክስ ዘርፉ ላይ ያለውን መዋቅራዊ አደረጃጀት፣ የሰው ኃይል፣ የመረጃ ልውውጦች በአጠቃላይ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ላይ ማነጽ ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም ይህ የሎጂስቲክስ ፖሊሲ ሲዋቀር ብሔራዊ የኢንፎርሜሽን እና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ፖሊሲና ስትቴጂን እንደ መነሻ ተጠቅሟል፡፡

### 1.2.7. የሀገራችን የሎጂስቲክስ አገልግሎት አከናዋኞች

#### ሀ. <u>የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርት አገልግሎ ድርጅት /ኢባትሎአድ/</u>

ኢባትሎአድ አራት የተለያዩና በሎጂስቲክስ ስራ መስክ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ድርጅቶችን በማዋሃድ የተቋቋመ የመንግስት የልማት ድርጅት ነው፡፡ እነዚህ አገልግሎቶችም የባህር ትራንስፖርት፣ የደረቅ ወደብ አገልግሎት፣ የትራንዚት ወይም የዕቃ ማስተላለፍ /Freight Forwarding/ አገልግሎት እና የጭነት ትራንስፖርት አገልግሎቶች ናቸው፡፡

ኢባትሎአድ እነዚህን አገልግሎቶች አጣምሮ ሲሰራ ቢቆይም እንደ አንድ ግዙፍ የልማት ድርጅት የሆነ የንግድ ተቋም የማይናቅ ውጤት እና አስተዋጽኦ ያደረገ ቢሆንም የሚፈለገውን ያህል ውጤት እያስመዘገበ የሚገኝ ተቋም አይደለም፡፡ ይልቁንም ተቋሙ ካለው አጠቃላይ ድርጅታዊ መዋቅር ጀምሮ ካሉት የሰው ኃይል አደረጃጀቶች እና ተቋሙ ከተሰማራበት ዓለም ዓቀፍ ተወዳዳሪነትን የሚጠይቅ የንግድ ዘርፍ አንጻር መሰረታዊ ለውጦች የሚያስፈልጉት ተቋም ነው፡፡

የዚህ ግዙፍ ተቋም በርካታ መዋቅራዊና የስራ አፈጻጸም ችግሮች ድርጅቱን ተወዳዳሪ እንዳይሆን ከማድረጋቸውም በላይ ድርጅቱ በዘርፉ ወሳኝ የሆኑ የአገልግሎት መስኮችን በብቸኝነት በመያዙ ምክንያት የግል ባለሃብቱን ተሳትፎ ለማበረታታት፣ የቴክኖሎጂና የእውቀት ሽግግር ለማምጣትና የካፒታል ፍሰትን ለማጎልበት የማያስችል ሆኖ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም ይህ የሎጂስቲክስ ፖሊሲ የዚህን ተቋም አጠቃላይ ሁኔታዎች መነሻ አድርጓል፡፡

### ለ. የግል ባለሃብቱ

የሎጂስቲክስ አገልግሎት ዘርፉ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ በባህሪይው በውድድር ላይ የተመሰረተ፣ ፈጣንና ቀልጣፋ መሆን ያለበት ከመሆኑም በላይ በቴክኖሎጂ የተደገፈና የተለያዩ የትራንስፖርት ዓይነቶች (Modes of Transports) ማለትም የባሕር፣ የአየር፣ የወደብ አገልግሎት፣ የፖስታ አገልግሎት በተቀናጀ መልኩ የሚሰጥ ብቁ የሰው ኃይል የሚሳተፍበት ሊሆን ያስፈልጋል፡፡ የሃገራችን የሎጂስቲክስ ዘርፍ ግን የግል ባለሃብቱን በመጋበዝና በማሳተፍ ረገድ ገና ብዙ ርቀት መጓዝ ይጠበቅበታል፡፡

በአንጻሩ ደግሞ በሎጂስቲክስ የአገልግሎ ዘርፍ ለመሳተፍ በርካታ የግል ባለሃብቶች ፍላጎት ያሳዩ ቢሆንም ባሉት የአሰራርና የህግ ማዕቀፎች ምክንያት ይህን ፍላጎት ማስተናገድ ሳይቻል ቆይቷል፡፡ የግል ባለሃብቱ በዚህ ዘርፍ መሳተፍ ደግሞ በዘርፉ ተወዳዳሪነትንና ቀልጣፋ የአገልግሎት አቅርቦትን በማረጋገጥና ዘመናዊና ትርፋማ በመሆን ለሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች የሚኖረው ሚና መጎልበት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡ እናም የዚህ ፖሊሲ ሌላኛው መነሻ የሆነው ጉዳይ የግል ባለሃብቱን በዚህ ዘርፍ ለማሳተፍ የሚያስፈልገውን የፖሊሲ አቅጣጫ ለማስቀመጥ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

# የፖሊሲው ራዕይ፣ ዓላማዎች፣ መርሆዎች እና አስፈላጊነት

## 2.1. የፖሊሲው ራዕይ

ኢትዮጵያ ሀገራችን በሎጅስቲክስ አገልግሎት ስርዓት ከአፍሪካ ተወዳዳሪና ቀዳሚ፣ እንዲሁም ሀገራችን ካላት የጂኦግራፊ አቀማመጥ አንጻር ለአጎራባች አህጉራትም ዋና የሎጂስቲክስ መዳረሻ ሆና ማየት ነው፡፡

## 2.2. የፖሊሲው ዓላማዎች

የፖሊሲው ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

- የሎጂስቲክስ ዘርፉን አመራር፣ አደረጃጀት እና አሰራር ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ለማቀረብ በሚያስችል መልኩ ትራንስፎርም ማድረግ፡፡
- በሎጅስቲክስ መሰረተ ልማት ግንባታ እና አገልግሎት አሰጣጥ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ በማሳደግ ዘርፉ ለውድድር ክፍት እንዲሆን ማድረግ፣
- የሎጅስቲክስ ዘርፍ ለወጣቶች የስራ ዕድል በመፍጠር ከሌሎች የኢኮኖሚ መስኮች ጋር ተደጋጋፊ ሆኖ እንዲያድግ ማድረግ፡፡

## 2.3. የፖሊሲው መርሆዎች

ይህ የሎጂስቲክስ ፖሊሲ የሚመራባቸው መርሆዎች፡-

- የሎጅስቲክስ ዘርፉ በውድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ
- በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የታገዘ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና አስተማማኝ የሎጅስቲክስ አገልግሎት ስርዓት ማረጋገጥ

## 2.4. የፖሊሲው አስፈላጊነት

የሀገራችን የሎጂስቲክስ ስርዓት ለኢኮኖሚያችንና ሌሎች ወሳኝ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ያለውን ቁልፍ ሚና በአግባቡ እንዲወጣ ዘርፉ ሊደርስበት የሚፈለገው አጠቃላይ ግብ እና ለዘርፉ

Ministry of Transport ARCHIVE

የሚያስፈልጉትን የአደረጃጀትና ተያያዥ ጉዳዮች ለመወሰን የሚያስችል የፖሊሲ ውሳኔ ያስፈልገዋል፡፡

የሀገራችንን ኢኮኖሚ ለማጎልበት በየዘርፉ የተለያዩ የፖሊሲ ሰነዶች ተዘጋጅተው እየተተገበሩ ይገኛሉ፡፡ ይሁንና እነዚህ ፖሊሲ የተቀረጸላቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች ሲተገበሩ ለዘርፎቹ ትልቁን ሚና የሚጫወተው የሎጂስቲክስ ዘርፍ በፖሊሲ ካልተመራ ከዘርፉ ሊገኝ የሚገባውን ሀገራዊ ጥቅም ለማግኘት አይቻልም፡፡

ይህን ለማድረግ እንዲረዳ ታስቦ የሎጂስቲክስ ስትራቴጂ ሰነድ በ2011 ዓ.ም ጽድቆ ስራ ላይ የዋለ ሲሆን እዚህ ስትራቴጂ ላይ ያሉት ፖሊሲ ነክ ጉዳዮች የመንግስትን ፍላጎት ግልጽ አድርጎ በማስቀመጥ የሎጂስቲክስ ዘርፉን አገልግሎት በፖሊሲ መቅረጽ አስፈልጓል፡፡ በተለይም ደግሞ ከአጠቃላይ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ዘርፉ መሻሻል ጋር የኢትዮጵያን የመርከብ ባለቤት ሀገርነት ሆኖ እንድቀጥል ማድረግ፣ በዘርፉ የግል ባለሃብቱን ተሳትፎ ማጎልበት፣ የ"FOB" አሠራርን ማሻሻልን፣ የዘርፉንና የኢባትሎአድን አደረጃጀት ማሻሻልን ያካትታል፡፡ ስለሆነም በነዚህ አጠቃላይ ምክንያቶች ይህን የብሄራዊ የሎጂስቲክስ ፖሊሲ መቅረጽና ስራ ላይ ማዋል አስፈልጓል፡፡

Ministry of Transport

# ክፍል ሦስት
# የፖሊሲ ጉዳዮች

የሎጅስቲክስ ዘርፍ ፖሊሲዎች በዋናነት በሶስት ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ እነሱም የሎጅስቲክስ ዘርፍ አደረጃጀትን ዘርፉን ለመምራት በሚስችል መልኩ ማሻሻል፣ የዘርፉን አገልግሎቶች እና የግል ኦፐሬተሮች ተሳትፎ በማሳደግ ዘርፉን በውድድር እንዲመራ ማድረግ እና የሎጅስቲክስ አሰራሮችን በማዘመን ሀገራዊ የሎጅስቲክስ ብቃትን እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ ናቸው፡፡ ስለሆነም የሎጅስቲክስ ዘርፍ ፖሊሲዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 3.1. የሎጅስቲክስ ዘርፍ አደረጃጀት

የሎጅስቲክስ ሥርዓት ከመነሻ እስከ መድረሻ ባለው ሂደት ሶስት ፍሰቶችን ማለትም የዕቃ ፍሰትን፣ የፋይናንስ ፍሰትና የመረጃ ፍሰትን አቀናጅቶ፣ አስተሳስሮ የማቀድ፣ የመምራትና የመቆጣጠር አሠራር ነው፡፡ እንዲሁም የሎጅስቲክስ ሂደት የተለያዩ ባለድርሻ አካላትንና ተቋማትን የሚያሳትፍ ሥርዓት ነው፡፡ እነዚህ አካላትን በተቀናጀ መልኩ በሎጀስቲክስ ሥርዓቱ ውስጥ በጋራ የመሥራት የሎጅስቲክስ ዓላማን ለማሳካት በሁሉም ዘርፍ ትስስር የመፍጠር ጉዳይ ደግሞ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም የሀገራችንን የሎጅስቲክስ ቅንጅት ክፍተት ቁልፍ ችግርን ለመፍታት የሚያስችልና ዘርፉን በበላይነት የሚመራ የተቀናጀ አደረጃጀት እንዲኖር የማድረጉ አስፈላጊነት ጠቀሜታው የጐላ ነው፡፡

ስለሆነም በትራንስፖርት ሚኒስቴር ሰብሳቢነት የሎጅስቲክስ ዘርፍን በተቀናጀ መልኩ ለመምራትና ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ም/ቤት እንዲቋቋም፣ እንዲሁም የም/ቤቱ ሴክሬታሪ ሆኖ የሚያገለግል የሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት በሚኒስቴር መ/ቤቱ አማካኝነት የሎጅስቲክስ ስራ በሚመለከተው ተቋም ስር እንዲቋቋም፣ በከተሞች እና በክልሎች ያለውን የሎጅስቲክስ ሂደት የሚመራ የከተማ የሎጅስቲክስ ም/ቤት እና ክልላዊ የሎጅስቲክስ ም/ቤት ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ም/ቤቱ በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት እንዲቋቋም፣በዘርፉ ያሉ ተዋንያን ማለትም የአስመጪዎች፣የላኪዎች፣የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች እና የተቆጣጣሪ ተቋማት የሚወከሉበት የሎጅስቲክስ ማህበረሰብ የጋራ አደረጃጀት እንዲፈጠር በሀገራዊ ም/ቤቱ በኩል አስፈላጊው ድጋፍ እንዲደረግ ተወስኗል፡፡

Ministry of Transport ARCHIVE

## 3.2. የሎጅስቲክስ ዘርፍ አገልግሎት

### 3.2.1. የባህር ማጓጓዝ አገልግሎትን በተመለከተ ብሄራዊ የንግድ መርከብ አገልግሎት (National carrier) ማስቀጠል

የባህር ትራንስፖርት አገልግሎትን በሚመለከት መንግስት የሚከተለው የፖሊሲ አቅጣጫ ከሀገራችን ብሄራዊ ጥቅም ጋር የተሳሰረ እንደመሆኑ በጥንቃቄ የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ከባህር ትራንስፖርት አገልግሎት ጋር በተያያዘ በዚህ ሰነድ የታዩ ሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህም፡-

- ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የመርከብ ባለቤት ሆና ትቀጥል ወይም አትቀጥል?
- የመልቲ-ሞዳል የትራንስፖርት ሥርዓት በመተግበር የተገኘ ሀገራዊ ጠቀሜታ ከብቸኛው የሥርዓቱ አከናዋኝ (MTO) ጋር ያለው ትስስርና ሥርዓቱ ይቀጥል ወይስ አይቀጥል?
- የ ‹‹Free on Board›› እንዲሆን በማድረግ በባህር የማጓጓዝ ኃላፊነቱን በኢትዮጵያ ይከናወን ወይም ለገቢ ዕቃ አቅራቢዎች (suppliers) አሳልፎ ይሰጥ? ይህ ፖሊሲ ከመርከብ ባለቤትነት፣ ከመልቲ-ሞዳል ሥርዓት ትግበራና በዚህ ፖሊሲ ለአከናዋኙ ጥቅም ከማስገኘቱ በላይ የተገኘው ሀገራዊ ጠቀሜታ ይቀጥል? ወይስ አይቀጥል? የሚለው ጉዳይ የሚያካትቱ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት አገልግሎት የምታገኘው በኢባትሎአድ ኃላፊነትና በሌሎች የውጭ ሀገር ኩባንያዎች አማካይነት ነው፡፡ በኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ ኃላፊነት የሚጓጓዘው የጭነት መጠን ከሀገራችን አጠቃላይ የውጭ ንግድ ውስጥ 25% ያህል ሲሆን፣ የሚጓጓዘው በሁለት መንገድ ነው፡፡ እነርሱም፡-

1ኛ. **የራስ መርከብ በመጠቀም፡-** ኢትዮጵያ ባሁኑ ወቅት የ11 መርከቦች ባለቤት ስትሆን፣ በኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ አማካይነት ከሚጓጓዘው አጠቃላይ ጭነት ውስጥ በራስ መርከብ እየተጓጓዘ ያለው 20% ነው፡፡

2ኛ. **የውጭ ሀገር የመርከብ ኩባንያዎችን በመጠቀም፡-** በኪራይ (Charter)፣ የተወሰነ የመጫኛ ቦታ በመከራየት "SCA (Slot Charter Agreement)" እና መሰል አሠራሮችን በመተግበር በውጭ ሀገር የመርከብ ኩባንያዎች የሚጓጓዘው ደግሞ 80% ድርሻ አለው፡፡

የትራንስፖርት ሚኒስቴር Ministry of Transport

ከዚህ ዳታ መገንዘብ እንደሚቻለው የባህር ትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፉን ትርፋማ ለማድረግ ከተፈለገ በዚህ ረገድ የመንግስትን የፖሊሲ ፍላጎት በግልጽ በመለየት እና ለዘርፉ የሚሰጠውን ድጋፍ በማስቀጠል፣ በዋናነትም ለኢባትሎአድ ከአደረጃጀትም ሆነ ከአገልግሎት አተገባበር አንጻር የተለያዩ ስልቶችና ስትራተጂዎች በመንደፍ አትራፊ ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ ይጠበቃል፡፡

ስለሆነም ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የመርከብ ባለቤት ወይም ብሄራዊ የንግድ መርከብ ባለቤት እና የ‹‹ NVOCC (None Vessel Owner Common Carrier›› አገልግሎት ሰጪ ሆና እንድትቀጥል መደረጉ የመንግስት ፍላጎት በመሆኑ በዚሁ አቅጣጫ የሚተገበር ይሆናል፡፡

### 3.2.2. የደረቅ ወደብ ልማት እና አገልግሎት

#### 3.2.2.1. <u>የደረቅ ወደብ ልማትና አገልግሎትን ለግል ባለሀብቶች ክፍት ማድረግ</u>

በሀገራችን ውስጥ የሚገኙት ደረቅ ወደቦች በሙሉ የተገነቡት በመንግሥት ማለትም በኢባትሎአድ አማካይነት ነው፡፡ በእነዚህ ደረቅ ወደቦች የሚሰጡት አገልግሎቶችም እስከአሁን ድረስ የሚከናወኑት በኢባትሎአድ ብቻ ነው፡፡ ይህም ማለት ደግሞ የግል ድርጅቶች በደረቅ ወደብ ልማትም ሆነ አገልግሎት መስጠት ውስጥ ተሳትፎ የላቸውም ማለት ነው፡፡ ይህ አሰራር ደግሞ ለውድድር ዝግ በመሆኑም የተለያዩ አዳዲስ ቀልጣፋና ዘመናዊ አሰራሮችን ለማስተዋወቅ እክል ስለሚፈጥር ዘርፉ የበለጠ ትርፋማ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡

ስለሆነም በቀጣይ የግል ባለሀብቶች በነባር ደረቅ ወደቦችም ሆነ አዲስ ደረቅ ወደብ በማልማት ሂደት ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ የመንግስት ፍላጎት ነው፡፡ ይህም የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ከማሳደጉ ባለፈ አስመጪና ላኪዎች ኦፐሬተሮችን አወዳድረው እንዲጠቀሙ እና በዘርፉ የውድድር ሜዳን ስለሚያሰፋ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ በመንግስት ታምኖበታል፡፡ በመሆኑም የደረቅ ወደቦችን ለግል ባለሀብቶች ክፍት ማድረግ የመንግስት ፍላጎት ስለሆነ በዚሁ አቅጣጫ አስፈላጊ የሆኑ የህግ ማዕቀፎች እና አሰራሮች ተዘርግተው ተግባራዊ የሚደረጉ ይሆናል፡፡

#### 3.2.2.2. በደረቅ ወደቦች የጋራ አጠቃቀም (common use facility) አሠራር መዘርጋት

በመንግስት በተገነቡት የደረቅ ወደቦች ውስጥ የግል ባለሀብቶች ገብተው አገልግሎት የሚሰጡበት አሠራር እስከአሁን ድረስ አልነበረም፡፡ በመሆኑም ደረቅ ወደቦቹ በአንድ ኦፐሬተር አገልግሎት ሰጪነት ብቻ የተያዙ ናቸው፡፡

ነገር ግን ይህ ዓይነቱ የደረቅ ወደቦች አጠቃቀም ውድድርንና ቀልጣፋ የአሰራር ስርዓትን የማያበረታታ መሆኑ በመንግስት ስለታመነበት በደረቅ ወደቦች እሴት የሚጨምሩ አገልግሎቶችን ለመስጠት ወደሚያስችል የሎጂስቲክስ ማዕከልነት (Logistics hub) ትራንስፎርም በማድረግ በርካታ ኦፐሬተሮች አገልግሎት የሚሰጡበት (multi-user) እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለዚህም ባለቤትነቱ በኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ ስር ሆኖ በደረቅ ወደቦቹ የጋራ የአጠቃቀም አሠራር እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡

#### 3.2.2.3. ደረቅ ወደቦችን በጋራ (Joint Investment) ማልማትና ማስተዳደር

የሀገር ውስጥ ደረቅ ወደቦችና ተርሚናሎች ይበልጥ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት የሚሰጡ እንዲሆኑ፣ እንደዚሁም የሀገራችን የሎጅስቲክስ አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል ሂደት የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ለማድረግ ኢንቨስትመንት ይጠይቃል፣ የዘርፉ ዕውቀት (sector knowledge) ባለቤት መሆንንም እንዲሁ በጣም ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ ከግል ባለሀብቶች በጥምር ኢንቨስትመንት (Joint Investment) ይሁን በሌሎች የጋራ አሠራሮች (partmership arrangements) ስርዓቶች እንዲሠራ ይደረጋል፡፡

### 3.2.3. የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት

#### 3.2.3.1. የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት አከናዋኝ (Multi-Modal Transport Operator) ለግል ባለሀብቱ ክፍት ማድረግ

የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ለሀገራችን ያበረከተው አስተዋጽዎ ተገምግሞ በውጭ ምንዛሪ ሊወጣ ይችል የነበረ ወጪ በመቀነስ ረገድ ዓይነተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ በዓመት በአማካይ ከ20 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ያላነሰ ወጪ ለመቀነስ አስችሏል፡፡ ስለሆነም የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ በሌላ በኩል የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት አሁን በአንድ ኦፐሬተር ማለትም በኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ

ብቻ እየተሰጠ ቢሆንም ከዚህም በተጨማሪ ሥርዓቱ አሁን በአለው አሠራር በዋናነት የባህር ማጓጓዣን መሠረት አድርጎ እየተተገበረ ከመሆኑ አንጻር ሌሎች የትራንስፖርት ዓይነቶችን ማለትም የባሕር ትራንስፖርትን፣ የባሕር ወደብን እና የአየር ትራንስፖርትን በማቀናጀት በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ኦፕሬተርነት ተሳታፊ በማድረግ ሽፋኑን በማሳደግ የሀገራችንን ተጠቃሚነት ይበልጥ ለማስፋት ተጨማሪ የመልቲ ሞዳል ኦፐሬተሮችን መፍጠር ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ በመንግስት ታምኖበታል፡፡

ከላይ በቀረበው ማብራሪያ መሰረትም ከኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ በተጨማሪ የመልቲ ሞዳል ኦፐሬተር ፈቃድ በአጭር ጊዜ ለሀገር ውስጥ ባለሃብቶች፤ በቀጣይ ደግሞ ለውጭ ባለሀብቶች መስጠት የተሻለ አማራጭና የሚያስገኘውም ጠቀሜታ የጐላ በመሆኑ ይኸው ተግባራዊ እንዲደረግ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡

## 3.3. የሎጅስቲክስ ዘርፍ አሰራር

### 3.3.1. በሥራ ላይ ያለውን የ"FOB" አሰራር እና አከናዋኝ አሰያየም ማሻሻል

የ "FOB" መመሪያ አከናዋኝ አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ. ብቻ ነው፡፡ ሆኖም መመሪያው ልዩ ሁኔታዎችን ለማካተት የሚያስችል ዕድል የሌለው በመሆኑ በአፈጻጸም ላይ በርካታ ችግሮች ይታያሉ፡፡ ስለሆነም የኢንዱስትሪ እቃ አምራች እና ላኪዎችን ለማበረታት ሲባል በተወሰነ ደረጃ የሌሎች የመርከብ ኩባንያዎችን የመጠቀም ዕድል እንዲያገኙ ለማድረግ፣ ያለ ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ. ፍቃድ አውቀውም ሆነ በስህተት በውጭ አገር መርከቦች ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡ አስመጪዎችን ለማረም በሚያስችል መልኩ ማሻሻል የመንግስት ፍላጎት ነው፡፡

የሀገራችን አስመጪዎች የጭነት መጠን ገና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑና በሀገር ደረጃም የ"Shipper Council" ተቋቁሞ የመደራደር አቅማችን ባላደገበት ሁኔታ የ"FOB" መመሪያ ማንሣቱ ጉዳቱ ዘርፈ-ብዙ ነው፡፡

ስለሆነም የ"FOB" መመሪያው ከታች የተዘረዘሩትን ነጥቦችና ሌሎች ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት መሻሻል ይኖርበታል፡፡ እነርሱም፡-

- የውጭ ሀገር ኢንቨስተሮች በኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ ብቻ እንዲጠቀሙ እንዳይገደዱ ማድረግ፤



ARCHIVE
Ministry of Transport

- የ"Wavier" አሰጣጥ ማሻሻልና "flexible" እንዲሆንም ማድረግ፤
- የ"FOB" አከናዋኝ የሚሰጠው አገልግሎትና የአገልግሎት ዋጋ ለመቆጣጠር የሚያስችልና የተጠቃሚዎች እርካታን ለማሳደግ የሚያስችል አሠራር መዘርጋት፤
- የ"FOB" አከናዋኝ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣ ለመጨመርና ለመቀነስ የሚያስችል ሆኖ እንዲቀረጽ ይደረጋል፡፡

## 3.3.2. የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት እና ሎጀስቲክስ አገልግሎት ድርጅትን /ኢባትሎአድ/ አሰራር እና አደረጃጀት በማሻሻል ትራንስፎርም ማድረግ

ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ. በሀገሪቱ ብቸኛው የመልቲሞዳል እና የደረቅ ወደብ እንዲሁም የ FOB ግገር ሥርዓት አስፈጻሚ የመንግሥት ኦፕሬተር ነው፡፡ ስለሆነም ይህ ተቋም ዘርፉ ለግል ባለሀብቶች ክፍት ሲሆን በውድድር ሜዳው ብቁ ተወዳዳሪ እንዲሆን የሚያስችለውን አቅም መፍጠር ይኖርበታል፡፡

አሁን ባለው ሁኔታ ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ. በአብዛኛው በመንግስት በሚወሰን አሠራር የሚመራ ተቋም ነው፡፡ ተቋሙ ከሌሎች ዓለም አቀፍ መሰል ኩባንያዎች ጋር ለመወዳደር የሚያስችለውን ፈጣን ውሳኔ፣ ቀላል የግገር ሥርዓት እና አማራጭ ቢዝነሶችን ተግባራዊ በማድረግ ሂደት እጅግ አዝጋሚ ነው፡፡ ይህም የደንበኞችን ፍላጎት በማርካት እና ሎጀስቲክሱን በማዘመን ለሀገር የሚያበረክተውን አስተዋጽዎ ውሱን እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

ስለሆነም የቦርድ አሰያየም ሥርዓት፣ የግገር ሥርዓቱ እና የሠራተኛ ቅጥር ሥርዓት እንዲሻሻል እና በአጠቃላይ ውጤታማና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችለው ሪፎርም እንዲያደርግ የመንግስትም ፍላጎት ስለሆነ የኢባትሎአድ አደረጃጀት በዚሁ አቅጣጫ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡ በዚህም መሰረት፡-

1. ይህ የመንግሥት የልማት ድርጅት ብሄራዊ ሀብትነቱን ይበልጥ ለማረጋገጥ የተወሰነ ድርሻ ለጭነት ባለቤቶችና በዘርፉ የግል ሎጀስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች አክሲዮን መሸጥ እንዲችል፣
2. አዲሱ ተቋም ዘመናዊ እና ዓለምአቀፋዊ አሰራር ልምዶችን ማግኘት እንዲችል በተለዩ የስራ መስኮች ከታወቁ ዓለም አቀፍ የሎጅስቲክስ ኩባንያ ጋር በ JV ወይም መሰል ቅንጅት እንዲሰራ፣

3. በአጠቃላይ በአፍሪካ ግንባር ቀደም እንዲሆን የሚያስችለው መዋቅራዊ አደረጃጀቱ የተሟላ ቁመና ያለው ተቋም በማድረግ እንደ Holding Company የሚደራጅበት አሰራር ይዘረጋል፡፡

# ክፍል አራት

# የፖሊሲ ማሳፈጸሚያ ስልቶች

በፖሊሲ ሰነዱ በክፍል አራት ላይ የተገለጹትን ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች እና የፖሊሲ ግቦች ሊተገበሩ በሚችሉበት አግባብ ወደ መሬት ለማውረድ ብሔራዊ የሎጂስቲክስ ምክር ቤት እንደየ አግባቡ አቅጣጫ የሚሰጥባቸው የሚከተሉትን የማስፈጸሚያ ስልቶች ተመላክተዋል፡፡

## 4.1. የሎጅስቲክስ ዘርፍ በተቀናጀ አግባብ ለመምራት የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር

4.1.1. በትራንስፖርት ሚኒስቴር ሰብሳቢነት የሎጅስቲክስ ዘርፍን በተቀናጀ መልኩ ለመምራት የሚያስችል ውሳኔ ሰጪ ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ም/ቤት እንዲቋቋም ማድረግ፤ እንዲሁም የም/ቤቱ ሴክሬታሪ ሆኖ የሚያገለግል የሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ጽ/ቤት በሚኒስቴር መ/ቤቱ አማካኝነት እንዲቋቋም ማድረግ፣

## 4.2. የ ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ. አደረጃጀት ትራንስፎርም ማድረግ

4.2.1. ኢ.ባ.ት.ሎ.አ.ድ. ብሄራዊ ሀብትነቱን ይበልጥ ለማረጋገጥ የተወሰነ ድርሻ ለጭነት ባለቤቶችና በዘርፉ የግል ሎጀስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች አክሲዮን የሚሸጥ አሠራር እና ሥርዓት መዘርጋት፣ ዘመናዊ እና ዓለምአቀፋዊ አሰራር ልምዶችን ማግኘት እንዲችል በተለዩ የስራ መስኮች ከታወቁ ዓለም አቀፍ የሎጅስቲክስ ኩባንያ ጋር በ JV ሚሰራበትን ሥርዓት መዘርጋት፣ በአፍሪካ ግንባር ቀደም እንዲሆን የሚያስችለው መዋቅራዊ አደረጃጀቱ የተሟላ ቁመና ያለው ተቋም በማድረግ እንደ Holding Company የሚሆንበትን ሪፎርም እና ሥርዓት መዘርጋት፡፡

ትራንስፖርት ሚኒስቴር
ARCHIVE
Ministry of Transport

## 4.3. የሎጀስቲክስ ዘርፍ አገልግሎቶች የመመሪያ ማሻሻያዎች ማድረግ

### 4.3.1. የደረቅ ወደብ ልማትና አገልግሎት ለግል ባለሀብቶች ክፍት ማድረግ

የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በብቸኝነት የያዘውን የደረቅ ወደብ አገልግሎት ለግል ባለሀብት ክፍት ለማድረግ የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ እና የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፡፡

### 4.3.2. የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት አከናዋኝ (Multi-Modal Transport Operator) ለግል ባለሀብቱ ክፍት ማድረግ

የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት በብቸኝነት የያዘውን የመልቲ- ሞዳል ትራንስፖርት አከናዋኝ አገልግሎት ለሌሎች የአገር ውስጥ አከናዋኞች ክፍት ለማድረግ የሚያስችል የሁለትዮሽ ስምምነት ማሻሻል፣ የህግ ማዕቀፍ እና የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፡፡

## 4.4. የሎጀስቲክስ ዘርፍ አሠራር ላይ ማሻሻያዎች ማድረግ

በ1990 ዓ.ም እና በ1992 ዓ.ም በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የኢኮኖሚ ዘርፍ ጉዳዮች በቁጥር ጠ80- አጠ74/01/03 እና መደ1-811/4 እንደ ቅደም ተከተላቸው የወጡ የ "FOB" ፖሊሲ ከወቅቱ የአገራችን የኢኮኖሚ ፖሊሲ አቅጣጫ አንጻር እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡

ትራንስፖርት ሚኒስቴር
Ministry of Transport

# ክፍል አምስት

# ልዩ ልዩ ጉዳዮች

## 5.1. የፖሊሲው ክትትልና ግምገማ

የሎጂስቲክስ ፖሊሲውን የሚያስፈጽመው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. ትራንስፖርት ሚኒስቴር ሲሆን በስሩ ያሉ ተጠሪ ተቋማት በተዋረድ የፖሊሲውን አፈጻጸም የመከታተል ኃላፊነት እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

የፖሊሲውን አፈጻጸም በየጊዜው ክትትልና ግምገማ ይደረጋል፡፡ በዚህ ሂደትም ይህን ፖሊሲ የሚቃረኑ አዋጆች፣ ደንቦች መመሪያዎች ወይም አሰራሮች ከተገኙ በሂደት ከዚህ ፖሊሲ ጋር እንዲጣጣሙ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም የተቋማት አደረጃጀቶች ይህን ፖሊሲ ለማስፈጸም እክል የሚሆኑ ከሆነ አደረጃጀቶቹ በዚህ ፖሊሲ ግብና አቅጣጫ መሰረት እንዲዋቀሩ ይደረጋል፡፡

## 5.2. የባለድርሻ አካላት ሚና እና ተሳትፎ

ይህን የሎጂስቲክስ ፖሊሲ ለማስፈጸም የበርካታ ባለድርሻ አካላት ሚና ወሳኝነት አለው፡፡ ስለሆነም በዚህ ፖሊሲ የአተገባበር ሂደት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በሙሉ በዚህ ፖሊሲ ስትራቴጂያዊ አፈጻጸም ላይ ሚና እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

## 5.3. ቀጣይ አቅጣጫዎች

ይህ ፖሊሲ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ከጸደቀበት ዕለት ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡ ፖሊሲው የተቀረጸውም ቀደም ብሎ በ2011 ዓ.ም ከጸደቀውና ለ10 ዓመት እንዲተገበር ተቀርጾ እስከ 2021 ዓ.ም ድረስ ከሚቆየው የሎጂስቲክስ ስትራቴጂ ሰነድ ጋር እንዲጣጣም ተደርጎ ስለሆነ ይህ ፖሊሲ ከጸደቀበት ጊዜ አንስቶ እስከ 2021 ዓ.ም ድረስ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

የትራንስፖርት ሚኒስቴር
ARCHIVE
Ministry of Transport